# ድርቅ: ለጋራ ችግር የጋራ መፍትሄ ያሻል

ታከለ አለሙ

በዋነኛነት ተከታታይ በሆነ ሁኔታ በዘመንና ግዜ ልዩነት ለሚከሰተው ድርቅ ተጋላጭ የሆነውን አርብቶአደሩን በቆላማ ቦታዎች የሚኖረውን አርሶ አደር ድርቁን ከመቋቋም አልፎ ወደፊት ቢከሰት እንዴት አድርጎ መመከት እንዳለበት ሰፊ ልምዶች የተቀመሩ ሲሆን ስራውም በተጠናከረ ሁኔታ በመካሄድ ላይ ይገኛል፡፡

ሰፋፊና ትላልቅ የውሀ ጉድጓዶች፤ የአፈር እቀባ ስራና የመስኖ ልማት፤ የደን ልማት ስራዎች፤ ከባድ ዝናብ በሚዘንብበት ወቅት ውሀውን ጠልፎ የማስቀረትና ወደመሬት ማስረግ አካባቢው እርጥበት እንዲያገኝ የሚያደርገው ሲሆን በሂደትም የአካባቢውን የአየር ንብረት ይለውጠዋል፡፡ የተክሎች የተለያየ ዛፎች ማደግና መስፋፋት በረሀማነትን ከመከላከልም አልፎ በተለይ በተራራማዎች አካባቢ ምንጮችን የማፍለቅ አቅም አለው፡፡

እነዚህንና ሌሎችንም መስረት ያደረገ ትምህርት በባለሙያዎች አማካኝነት ለአርሶ አደሩ እየተሰጠ ሁኔታዎችን ለመለወጥ በሁሉም ክልሎች ከፍተኛ ስራ በመሰራት ላይ ይገኛል፡፡ የመሬቱ ደርቆ መሰነጣጠቅ፣ የውሀ ሙሉ በሙሉ በአንዳንድ አካባቢዎች አለመኖርና መጥፋት ወዘተ ድርቁን የከፋ በማድረግ በሰውና በእንሰሳት ላይ ከፍተኛ ችግርና አደጋ ያስከትላል፡፡ ሰውም ሆነ እንሰሳት፣ ተክሎችም ጭምር ካለውሀ የመኖር ተስፋና እድል የላቸውም፡፡

ውሀ አጠር በሆኑ አካባቢዎች የሚደረገው የጥልቅ ጉድጓድ ቁፋሮው በሁሉም ክልሎች በስፋት መቀጠል ያለበት ቀዳሚ ተግባር ነው፡፡ ዘዴው እጅግ በጣም ብዙ ሺህ ዘመናትን ያስቆጠረ ሲሆን ዛሬ አደጉ የሚባሉት ሀገሮች ጥንት የሚጠቀሙት በውሀ ጉድጓድ እንደነበር ይታወቃል፤ ለከብቶች መኖ፤ ሳር ማሳደጊያ፤ ለመጠጥ ውሀ፤ ለቤት አገልግሎት፤ ለአትክልት ልማት በሰፊው ሲገለገሉበትም ኖረዋል፡፡ ዛሬም በውጭው አለም ገጠራማ አካባቢዎች በስፋት ይሰራበታል፡፡

ይሄ አዋጪና ዋስትና ያለው ዘዴ በዘመናዊ ሁኔታ ታግዞ ቢሰራበት ለእኛም በረሀማ አካባቢዎች ዘለቄታዊ መፍትሄ ያመጣል፡፡ በሀገራችን በተለይ የበረሀ ነዋሪውን አርብቶአደር የልማት ተጠቃሚ ለማድረግ ከ200 ሚሊዮን ዶላር በላይ በሆነ ወጪ የተለያዩ የልማት ስራዎች በመከናወን ላይ ይገኛሉ፡፡ የአርብቶ አደሩን የድርቅ ተጋላጭነት ለመቀነስና የምግብ ዋስትናቸውን በዘላቂነት ለማረጋገጥ በአገር አቀፍ ደረጃ በተዘጋጀው የ5 ዓመት ፕሮግራም የተጠቀሰው ወጪ ተደርጎበት ድርቅን ለመቋቋምና ተጋላጭነትን ለመቀነስ የሚያስችል ስራዎች እየተሰሩ መሆናቸውን የፌደራል ጉዳዮችና አርብቶ አደር አካባቢ ልማት ሚኒስቴር ገልጾአል፡፡

የፌደራሉ መንግስት ባቋቋመው የልዩ ድጋፍ ቦርድ በምክር ቤቱ የአርብቶ አደሩ ቋሚ ኮሚቴ ተደራጅቶ የክልሎችን ችግር ለመፍታት ድጋፍ እየሰጠ ይገኛል፡፡ በኢትዮጵያ ሶማሌና በአፋር፣ በደቡብና በኦሮሚያ ክልሎች የሚገኙ አርብቶ አደሮችን የከርሰ ምድርና የገጸ ምድር ውሀ እንዲያገኙ በማድረግ፤  የእንስሳት ሀብትን በማልማትና ከገበያ ጋር በማስተሳሰር ተጠቃሚ ለማድረግ ተሰርቷል፤ እየተሰራም ነው። የውሀ፣ ትምህርትና የጤና አገልግሎት ተደራሽነትን ከማሻሻል ረገድ አበረታች ውጤቶች መመዝገባቸውንም የሚኒስቴሩ ማሕበረሰባዊ ፕሮጀክት ኃላፊ አቶ ስዒድ ዑመር  አስረድተዋል፡፡ የመጠጥ ውሀ ሽፋንን በተመለከተ  በኦሮሚያ አርብቶ አደር 68 በመቶ፣ በአፋር 63 በመቶ፣ በኢትዮጵያ ሱማሌ 62 በመቶ እና በደቡብ 51 በመቶ የደረሰ መሆኑ ተገልጾአል፡፡ የመሰረታዊ ጤና ሽፋን በሶማሌ 88፣ በአፋር 89፣ በኦሮሚያ አርብቶ አደሮች 78 እና የደቡብ 92 በመቶ ደርሷል፡፡ የእንስሳትን ጤና ሽፋን በተመለከተም በኦሮሚያ 81፣ በደቡብ 72፣ በአፋር 67 እንዲሁም በኢትዮጵያ ሱማሌ 63 በመቶ  መድረሱን ሀላፊው ገልጸዋል፡፡ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ሽፋን፣ በተለይም በኢትዮጵያ ሱማሌ 65 በመቶና በአፋር 59 በመቶ መድረሱን ገልጸዋል፡፡ በሚኒስቴሩ አስተባባሪነት ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ የሚገኘው የአርብቶ አደሩ ማሕበረሰብ ልማት ፕሮጀክት በአርብቶ አደሩ ክልሎች የተጀመሩ ሰፋፊ የልማት ስራዎችን በስፋት እያካሄደ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ወደወቅታዊው ችግራችን፣ ወደድርቁ እንምጣና አንዳንድ ነገሮችን እናንሳ።

በፌደራል መንግስቱና በክልል መንግስታት ድርቁን ለመመከትና ለመቋቋም የቀን ከለሊት ስራዎች እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡ ምግብ፣ ውሀና መድሀኒት በማድረስና በማሰራጨት ለድርቅ ተጋላጭ ለሆነው ሕብረተሰብ  እለት በእለት እየደረሱለት ይገኛሉ፡፡

የአርብቶ አደሩ የልማት ፕሮጀክት ባለፉት 13 ዓመታት በ1ሺ 145 ወረዳዎች ከ430 ሚሊዮን ዶላር በላይ በሆነ ወጪ 4 ነጥብ 5 ሚሊዮን አርብቶ አደሮችን የማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግሎቶች ተጠቃሚ በማድረግ የገቢ አቅማቸውን እያሳደገ ይገኛል፡፡ ችግሩን ከስሩ ለመቅረፍ ባለመቻሉ በዚህ ዓመትም የድርቅ ተጋላጭ ሆነዋል፡፡ ድርቁ በተከሰተበት ቦታ አስከፊ አደጋ እንዳይደርስ በሚደረገው ርብርብ ሁሉም ዜጋ ከመንግስት ጎን ቆሞ የአቅሙን በማድረግ እገዛውን መስጠት ይጠበቅበታል፡፡

የልማት አጋሮች፣ ኢንቨስተሮች . . . የገንዝብ አቅም ያላቸው ሁሉ እጃቸውን ይዘረጉ ዘንድ የሚል ጊዜ ቢኖር ግዜው አሁን ነው፡፡ ሀምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክሙ ለሀምሳ ሰው ደግሞ ጌጡ እንዲሉ ችግሩ ለመንግስት ብቻ የሚተው ሳይሆን የሁሉም ዜጋ የጋራ ጉዳይ በመሆኑ ሁሉም ወገን የየራሱን ካበረከተ ቸግሩን ለመቅረፍ በእርግጠኝነት ይቻላል፡፡

በመላ አገሪቱ ለዘለቄታው ድርቅን መቋቋም የሚችል ዓቅም ለመፍጠር እየተካሄደ ያለው ጥረት ተጠናክሮ መቀጠሉን የፌደራል መንግሥት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽህፈት ቤት  ባወጣው ሳምንታዊ መግለጫ አስታውቆአል፡፡ በአሁኑ ወቅት ከ22 ሚሊዮን በላይ ህዝብ በተፋሰስ ልማት ስራ ላይ ተሰማርቶ እየሰራ እንደሚገኝ፤ መንግስት ድርቅ በተከሰተባቸው አካባቢዎች ያለውን ችግር በጊዜያዊነት ለመፍታት በዋናነት በራሱ አቅም የጀመራቸውን ስራዎች አጎልብቶና አጠናክሮ እንደሚቀጥል፣ ዓለም አቀፍ ተቋማትና ወዳጅ ሀገራትም ችግሩን ለመቋቋም በሚደረገው ጥረት የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ማስተባበሩን እንደሚገፋበት ገልጾአል፡፡

ድርቁ በተከሰተባቸው አካባቢዎች ያለው ማሕበረሰብ እና መላው ሕዝባችን እያደረጉት ያለውን ርብርብ እንዲሁም ድርቅን በዘላቂነት ለመቋቋም በአገር አቀፍ ደረጃ ለሚደረገው የልማት ስራዎች ርብርብ እያሳዩ ያሉትን ሁሉ ተሳትፏቸውን የበለጠ አጠናክረው እንዲቀጥሉ ጠይቆአል፡፡ ዘንድሮ  በአንዳንድ ቆላማ የአርብቶ አደር አካባቢዎች ያጋጠመው ድርቅ  የሚያስከትለውን አደጋ ለመቋቋም የኢፌዴሪ መንግሥት፣ የክልል መንግሥታት፣ የየአካባቢው ማሕበረሰብ እና መላው ሕዝቡ የጋራ ርብርብ በማድረግ ላይ እንደሚገኙም አስምሮበታል፡፡  የፌዴራል እና የክልል መንግሥታት በጋራ ለ5 ነጥብ 6 ሚሊዮን ሕዝብ ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ እርዳታዎችን እያቀረቡ እንደሚገኙ፤ የመጠጥ ውሀ በቦቴ በማመላለስ፣ የእንስሳት መኖ አቅርቦት፤ የሕክምና አገልግሎት ለድርቁ ተጠቂዎች እየተሰጠ እንደሚገኝም መግለጫው ጠቅሶአል፡፡

በድርቅ በተጠቁት አካባቢዎች የሚኖሩ የአርብቶ አደር ልጆች ከቀኤያቸው ሳይርቁ ትምህርታቸውን መቀጠል እንዲችሉ ሁሉን አቀፍ ድጋፍ መንግስት እያደረገ እንደሚገኝ በዚህም የፌዴራል መንግሥት ከመደበው ሀብት በተጨማሪ ክልሎች የየራሳቸውን በጀት በመጨመር የትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራም በመጀመሩ ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ማድረግ መቻሉን ገልጾአል፡፡

ድርቅን በመቋቋም ረገድ ባለፈው ዓመት የተገኙ በጎ ተሞክሮዎችን  በማስፋት የድርቅን ተጽዕኖና ዘላቂ ጉዳት የመቋቋም አቅምን ለማጎልበት እየተሰራ እንደሚገኝ ለአብነትም መስኖ ባለባቸው አካባቢዎች በፍጥነት የሚደርሱ የእንስሳት መኖዎችን የማልማት ሥራ እየተካሄደ መሆኑን መንግሥት ችግሩን በወሳኝነት በራስ አቅም ለመፍታት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት በተደረገ ርብርብ በድርቁ አንዳችም ዓይነት ሰብዓዊ ቀውስ እና ጉዳት ከመድረሱ በፊት አደጋውን መቋቋም መቻሉን የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን መግለጫ አውስቶአል፡፡  ድርቅን የመቋቋም ተግባራችንን ከዚያ በፊት ከነበረው ተመሳሳይ እንቅስቃሴዎቻችን የተለየ ያደረገው በወሳኝነት በራሳችን ሀገራዊ አቅም አደጋውን መቋቋም በመቻላችን ነው ሲልም አሰረድቷል፡፡

በተመሳሳይ፣ በኦሮሚያ ክልል ለሚገኙ የድርቅ ተጎጂዎች አስፈላጊው እርዳታ እየተከፋፈለ መሆኑን የክልሉ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን አስታወቆአል፡፡ ኮሚሽነሩ አቶ መኮንን ለሊሳ ለዋልታ እንደገለጹት በክልሉ የአርብቶ አደር ቆላማ አካባቢዎች የሚጠበቀው ዝናብ ባለመዝነቡ ምክንያት በቦረና፣ ጉጂ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ሐረርጌ፣ ምዕራብ ሐረርጌና ምዕራብ አርሲ ዞኖች በአጠቃላይ  2ሚሊዮን 49ሺ የሚደርሱ ሰዎች ለድርቅ ተጋልጠው እርዳታሽ እየተደረገላቸው ይገኛሉ።

በክልሉ በደጋማና ወይና አደጋ አካባቢዎች የክረምት ዝናብ በመዝነቡ አምና በክልሉ  ከነበረው 3ነጥብ 7ሚሊዮን የድርቅ ተረጂዎች ቁጥር እንዲቀንስ ማስቻሉን፤ በክልሉ ለድርቅ በተጋለጡ ዘጠኝ ዞኖች ለተረጂዎች  የመጠጥ ውሃ፣ ምግብና የእንስሳት  መኖ የማከፋፋል ሥራዎች ሲከናወኑ መቆየታቸውን፤ለእርዳታ ሥራ የሚውለውን 186 ሚሊዮን ብር የክልሉ መንግሥት የመደበ መሆኑን 97 ሚሊዮን ብር የፌደራል መንግሥት ድጋፍ ማድረጉን ኮሚሽነሩ አስረድተዋል፡፡

ቀደም ሲል የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ኢትዮጵያ ድርቅን ለመቋቋም እያደረገቻው ያለው ጥረት ሊታገዝ እንደሚገባው የገለጸ ሲሆን ኢትዮጵያ ያጋጠማት ድርቅ ከፍተኛነቱ የምስራቅ አፍሪካ አገራት እንኳን በጋራ ሊቋቋሙት የሚያዳግታቸው በመሆኑ ሀገሪቷ ድጋፍ ሊደረግላት ይገባል ሲሉ  ዋና ጸሐፊው አንቶኒዮ ጉቴሬዝ መግለጻቸው ይታወሳል፡፡

በመሆኑም፣ የችግሩ መጠን ይህን ያህል ከሆነ መፍትሄው ምን ይሆን? መፍትሄው አንድና አንድ ነው፤ ለጋራ ችግራችን የጋራ መፍትሄን መሻት፤ ከመንግስት ጎን በመቆም አስፈላጊውን ርብርብ ሁሉ ማድረግና ለተቸገሩ ወገኖቻችን ፈጥነን መድረስ። ይሄው ነው።